# ኢምፓወርድ ለርነርስ ኢኒሺዬቲቨ (Empowered Learners Initiative)፤ በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች ለቤተሰቦች

**ኢምፓወርድ ለርነርስ ኢኒሺያቲቨ (Empowered Learners Initiative) ምንድነው?**

ኢምባወርድ ለርነርስ ኢኒሺዬቲቭ (Empowered Learners initiative (ELi) በዲጂታል ያለውን ክፍተት ለመሙላት እና እያንዳንዱን የዲሲፒኤስ (DCPS) ተማሪዎች ስለ ቴክኖሎጂ ግንዛቤ ያላቸው እና ተሳታፊ የዲጂታል ዜጋ ለማድረግ በሜየር ቦውሰር (Mayor Bowser) የተጀመረ አጠቃላይ የሶስት ዓመት መርሃ ግብር ነው። መርሃ-ግብሩ ቴክኖሎጂ የማግኘት ዕድል ላይ ማተኮርን፤ የዲሲፒኤስን (DCPS) ስርዓተ- ትምህርት ማጎልበትን፤ የመምህራን የሙያ ማሻሻያ ስልጠና እና ለቤተሰቦች መረጃ እና መረጃ የማግኘትን ዕድል ያካትታል።

**መሳሪያዎቹን ማን ያገኛል?**

3ኛ፣ 6ኛ እና 9ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች በ 2019-2020 የትምህርት ዓመት በት/ቤት ውስጥ እንዲጠቀሙበት መሳሪያውን ያገኛሉ። በ 2020-2021 የትምህርት ዓመት በ3ኛ፣ 4ኛ 6ኛ፣ 7ኛ፣ 9ኛ እና 10ኛ ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች በት/ቤት ውስጥ እንዲጠቀሙበት መሳሪያውን ያገኛሉ። ግባችን በ 2021-2022 የትምህርት ዓመት ከ3ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ላለ እያንዳንዱ ተማሪ መሳሪያውን ማዳረስ ነው። ከቅድመ መዋዕለ ህጻናት እስከ 2ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች 3 ለ 1 መሳሪያ በሆነ ሬሾ ያገኛሉ።

**ተማሪዎች መሳሪያዎቻቸውን ወደቤት መውሰድ ይችላሉ?**

በ 2019-2020 የትምህርት ዓመት መሳሪያዎቹ ወደ ቤት አይወሰዱም። ይህንን ፖሊሲ በሚመለከት ከዓመት በኋላ ከቤተሰቦች፤ ሙራን አንድ ከሌሎች አጋርድ ድርጅቶች አስተያየት እንሰበስባለን።

ነገር ግን፤ ወላጆች የ ማይክሮሶፍት ኦፍስ (Microsoft Office) አካውንት ለመክፈት መመዝገብ የሚችሉ ሲሁን ተማሪዎችም እቤታቸው በሚገኘው የራሳቸው መሳሪያዎች ስራቸውን ከቤታቸው ሆነው መስራት ይችላሉ።

**ትምህርት ቤቶች መሳሪያዎቻቸውን መቼ ነው የሚቀበሉት?**

መሳሪያዎቹ በሁሉም ስምንት ዋርዶች በቅደም ተከተል የሚዳረሱ ሲሆን፤ ት/ቤቶች መቼ መሳሪያዎቻቸው እንደሚደርሷቸው በማርች ወር 2020 ዓ.ም. መረጃ ይደርሳቸዋል። እያንዳንዱ ት/ቤት መሳሪያዎቹ ከደረሱት በኋላ እንዴት ለተማሪዎች እንደሚያሰራጭ እቅዱን አጠናቋል።

**ት/ቤቶች ምን ዓይነት መሳሪያዎች ናቸው የሚደርሷቸው?**

ተማሪዎች ሃይብራይድ ላፕቶፕ እና ታብሌት (hybrid laptop and tablet) ማለትም ማይክሮሶፍት ሰርፌስ ጎ (Microsoft Surface Go) ይጠቀማሉ። ማይክሮሶፍት ሰርፌስ ጎ (Microsoft Surface Go) የተመረጠው በመጠኑ አነስ ያለ፤ ለብዙ ጊዜ የሚቆይ እና ካሜራ፤ ስታይለስ (stylus) ያለው እንዲሁም ባትሪው ለረጅም ጊዜ የሚቆይ በመሆኑ ምክንያትነው።

**የመሳሪያዎቹን ባለቤትነት ማነው የሚይዘው?**

ሁሉም መሳሪያዎች የዲሲፒኤስ (DCPS) ንብረቶች ናቸው። ይሁንና፤ ትምህርት ቤት ውስጥ እንዲጠቀሙባቸው መሳሪያዎቹ ለተማሪዎች ይመደባሉ።

**መሳሪያው ቢጠፋ፤ ቢሰረቅ ወይም ቢበላሽ ምን ይከሰታል?**

ሁሉም መሳሪያዎች ዋስትና አላቸው። ዲሲፒኤስ (DCPS) ተጨማሪ መሳሪያዎች በተጠባባቂነት ስላሉት መሳሪያዎች ቢጠፉ፤ ቢሰረቁ ወይም ቢበላሹ ወዲያውኑ መተካት እንችላለን።

**ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ለመሳሪያዎቹ የገንዘብ ሃላፊነት አለባቸው?**

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ለጠፉ ወይም ለተበላሹ መሳሪያዎች የገንዘብ ሃላፊነት የለባቸውም። ለራሳቸው የመማሪያ መሳሪያዎቻቸው ተማሪዎች በሃላፊነት መንፈስ ይገለገላሉ ብለን እናምናለን። ሁሉም ተማሪዎች መፈረም በሚገባቸው በተማሪ የቴክኖሎጂ ሃላፊነት የተሞላበት አጠቃቀም ስምምነት (*Student Technology Responsible Use Agreement)* በኩል ስለ መሳሪያዎቹ አጠቃቀም እና አያያዝ ከተማሪዎች ስለሚጠበቁ ነገሮች በግልጽ አስቀምጠናል።

ተማሪ እነዚህን ህጎች ካልተከተለ በዲሲፒኤስ (DCPS) የስራአት ህጎች አና ፖሊሲዎች ስር ያሉ ነገሮች ተግባራዊ የሚሆኑበት ሲሆን የዲሲፒኤስ (DCPS) መሳሪያዎችን እና የዲሲፒኤስ ግንኙነቶችን (DCPS network) የመጠቀም ዕድሎች ላይ ገደብ ሊጣልበት ይችላል። ቤተሰቦችም ስምምነቱን ከተማሪዎቻቸው ጋር ማየታቸውን ለማረጋገጥ ስምምነቱ ላይ እንዲፈርሙ ይጠየቃሉ።

**የተማሪ መሳሪያዎች ወደትምህር ቤት ከደረሱ በኋላ ለተማሪዎች አንድ የትምህርት ቀን ምን ይመስላል?**

የተማሪዎችን የመማር ተሞክሮዎች ለማጎልበት እነዚህን መሳሪያዎች መጠቀም እንዲችሉ መምህራን ስልጠና እና የስራአተ ትምህርት ድጋፍ ይሰጣቸዋል። እነዚህ መሳሪዋዎች ተማሪዎችን የማሳተፍ እና የተግባር ትምህርት ለተማሪዎች መስጠታቸውን የሚቀጥሉትን የመምህራንን ሙያዊ ችሎታዎች አይተኩም። ተማሪዎች እነዚህን መሳሪያዎች እየተማሩ ያሉትን ርዕስ በስፋት እንዲመራመሩ እና በርቀት ሆነው ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር በሚደረጉ ውይይቶች ላይ መሳተፍን፤ አንላይን ምርምር ማድረግን፤ ትምህርታቸውን በሚመለከት ለሌሎች ለማሳየት ቪዲዮ መቅረጽን እና ሌሎችንም አካቶ እራሳቸውን በአዲስ መንገድ ለመግለጽ ይጠቀሙባቸዋል።

**ተማሪዎች የቴክኖሎጂ መሳሪያዎቹን ካገኙም በኋላ መጻህፍትን መጠቀማቸውን ይቀጥላሉ?**

ተማሪዎች በዲሲፒኤስ (DCPS) ስርዓተ-ትምህርት ውስጥ አገልግሎት ላይ ያሉ መጻህፍትን የመጠቀም እድላቸውን ይቀጥላሉ። ይሁንና፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ ዲሲፒኤስ (DCPS) ባህላዊ የመማሪያ መጻህፍትን በተሻለ ሁኔታ ወቅታዊ ነገሮችን በሚሰጡት እና ሰፊ እና አሳታፊ ግብዓት ለማግኘት እድል በሚሰጡት ዲጂታል ግብዓቶች እየተካቸው ይገኛል።

---

**ለተጨማሪ መረጃ** [https://dcps.dc.gov/page/technology-dcps](https://dcps.dc.gov/page/technology-dcps) ይጎብኙ።